የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ-ህዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 5
ADDIS ABABA-24th Nov. 2006

## ማውጫ

የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............... ገጽ ፫ሺ፬፻፺፮

## CONTENTS

Information Network Security Agency Establishment Council of Ministers Regulations ..... ............... ..Page 3496

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፴/፲፱፻፺፱

**የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፴/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር፣

፩. "ቁልፍ ተቋም" ማለት ለኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት አደጋ የተጋለጠና በሚፈጠረው አደጋም በሀገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ጥቅሞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል ተቋም ነው፤

፪. "የኮምፒውተር ደህንነት" ማለት የኮምፒውቲንግ ፕላትፎርም ደህንነት ለማረጋገጥ ከኮምፒውተር አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ስጋቶችን መቆጣጠር ነው፤

Council of Ministers Regulations No. 130/2006

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR**

**THE ESTABLISHMENT OF THE INFORMATION NETWORK**

**SECURITY AGENCY**

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2006.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Information Network Security Agency Establishment Council of Ministers Regulations No. 130/2006".

2. *Definition*

In these Regulations, unless the context otherwise requires:

1. "critical infrastructure " means any infrastructure vulnerable to information communication network security threats having considerable impact to the social, economic or political interests of the country;
2. "computer security" means the control of risks related to computer use to secure computing platforms;

፫. "የኢንፎርሜሽን ሥርዓት" ማለት ኢንፎርሜሽን ለመሰብሰብ፣ ለመተንተን፣ ለመጠበቅና ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ የሚያስችል ሥርዓት ነው፤

፬. "የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ደህንነት" ማለት የኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ሆን ተብሎ ከታቀደ ወይም በስህተት ከሚፈጠር ያልተፈቀደ አጠቃቀም ወይም መረጃው በተከማቸበት፣ በሚተነተንበት ወይም በሚተላለፍበት ወቅት ከሚከሰት መረጃውን ከሚቀይር እንዲሁም የተፈቀደለት ተጠቃሚ አገልግሎት እንዳያገኝ ከሚያግድ ወይም ያልተፈቀደለት ተጠቃሚ አገልግሎት እንዲያገኝ ከሚያደርግ ጥቃት መከላከል ሲሆን ድርጊቱን ለመከታተል፣ ለመመዝገብና አጸፋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ይጨምራል፤

፭. "ኢንፎርሜሽን ሽብራ" ማለት የኢንፎርሜሽን መረብን በመጠቀም ሽብርና አመጽን የመቀስቀስ ተግባር ነው፤

፮. "የኢንፎርሜሽን ጦርነት" ማለት ኢንፎርሜሽንን፣ ኢንፎርሜሽንን መሠረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን፣ የኢንፎርሜሽን ሥርዓትና ኮምፒውተር ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገን መረብ ሆን ተብሎ ከሚታቀድ ጥቃት የመከላከልና አፀፋዊ ምላሽ የመስጠት ተግባር ነው፤

፯. "የኢንፎርሜሽን መረብ" ማለት በኢንተርኔት ወይም ኮምፒውተሮችን በማስተሳሰር ኢንፎር ሜሽን የማጓጓዝ የማከማቸትና የማሰራጨት ሥርዓት ነው፤

፰. "የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት" ማለት መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆነ አካላት የኢንፎርሜሽን መረብ አማካይነት ሊደርስ የሚችል አደጋን የማስወገድ ወይም የመቀነስ ተግባር ነው፤

፱. "ኤሌክትሮ ማግኔቲክ ኢነርጂ" ማለት ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ከሆኑ አካላት የሚመነጭ የኒውክሌር ኃይልን ሳይጨምር ለግንኙነት፣ ለመረጃ አሰባሰብና ለኢንፎርሜሽን ውጊያ ጥቅም ላይ የሚውል የጨረር ኃይል ነው፤

፲. "ሪሞት ሴንሲንግ" ማለት በሳተላይት ወይም በሌሎች በራሪዎች ላይ በሚገጠም የመረጃ ማሰባሰቢያ አነፍናፊ መሣሪያዎች በመጠቀም የሚካሄድ የኢንፎርሜሽን አሰባሰብ ዘዴ ነው፤

፲፩. "ኦፕትሮኒክስ" ማለት የተወሰነ የኤሌክትሮ ማግኔቲክ ኢነርጂ ክልልን በመጠቀም በካሜራ አማካይነት መረጃ የመሰብሰብ ዘዴ ነው፤

፲፪. "ክሪፕቶሎጂ" ማለት የኢንፎርሜሽን ደህንነትና እርግጠኝነትን ለማረጋገጥ ሲባል የሚከናወን የሶፍትዌርና ሀርድዌር ዲዛይንና የኮምፒውተር ቋንቋን የሚመለከት ሂሳባዊ ቀመር ነው።

፫. <u>መቋቋም</u>

፩. የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪. ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

3. "o\information system" means a system developed for purpose of collecting, processing, protecting and communicating information to users;

4. "information system security" means the protection of information systems against intentional or unintentional unauthorized assess or modification of information, whether in storage, processing or transit, and against the denial of service to authorized users or the provision of service to unauthorized users, including measures necessary to detect, document and encounter such treats;

5. "information terrorism" means the use of information network to instigate terror and violence;

6. "information warfare" means the act of protecting information, information based decision-making process, information system and computer based network from deliberate attacks and includes the act of counter attacking such threats;

7. "information network" means a system of transporting storage and dissemination of information via the internet or networked computer devices;

8. "information network security" means the control or mitigation of threats emanating from either governmental or non-governmental information networks;

9. "electro-magnetic energy" means radiation, other than nuclear energy generated from artificial or natural objects, used for communicaiton, gathering of information and information warfare;

10. "remote sensing" means a method of gathering information using remote sensor devices mounted to satellite or other space ships;

11. "optronics" means a method of gathering information using camera images within a specific range of electro -magnetic energy;

12. "cryptology" means mathematical model used in software and hardware design and computer language to ensure information security and authentication.

3. *Establishment*

1. The Information Security Agency(hereinafter the "Agency") is hereby established as an autonomous public agency having its own legal personality.

2. The Agency shall be accountable to the Prime Minister.

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭. ዓላማ

የኤጀንሲው ዓላማ ሀገሪቱ የኢንፎርሜሽንና የኢንፎርሜሽን መረብ ቴክኖሎጂንና ቴሌኮሙኒኬሽንን ለብሄራዊ ደህንነቷ ስጋት ሳያስከትል የሰላም፣ የዲሞክራሲና የልማት መርሃ ግብሮቿን ተግባራዊ ለማድረግ እንድትጠቀምበት ማስቻል ይሆናል።

፮. ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የኢንፎርሜሽንና የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት በሚመለከት መንግሥትን ማማከርና የፀደቁ ፖሊሲዎችና ህጎችን አፈጻጸም መከታተል፤

፪. በኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነትና የኢንፎርሜሽን ጦርነት ቴክኖሎጂዎች መስክ በጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ አቅም መፍጠርና በዘርፉም የጥናት፣ የዲቨሎፕመንት፣ የዲዛይን፣ የሙከራና ግምገማ ሥራዎችን ከግልና መንግሥታዊ መሰል ተቋማት ጋር አቀናጅቶ መፈጸም፤

፫. የኮምፒውተር መረብ፣ የኢንፎርሜሽን ስርዓትና የኤሌክትሮ ማግኔቲክ ኃይል አጠቃቀምንና የኢንፎርሜሽን ጦርነትን በሚመለከት የፖሊሲ፣ የህግ፣ የዕውቀትና የሌሎች ጉዳዮች ብሔራዊ ቅንጅት የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

፬. በሲግናልና ቴክኒካል ኢንፎርሜሽን እንዲሁም በክሪፕቶሎጂ በጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረተ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ለተለያዩ መንግሥታዊ የጸጥታ ተቋማት መስጠት፤

፭. የሪሞት ሴንሲንግ ካሜራዎችንና የተለያዩ ማግኔቲክ፣ ግራቪቲና የኤሌክትሮ ኦፕቲካል አነፍናፊዎችን በመጠቀም የሚደረግ ማንኛውም የዳታ አሰባሰብ፣ ትንተና፣ ሥርጭትና ዳታ ባንክ የመገንባት ተግባር ብሔራዊ የመረጃ ደህንነት ደረጃዎችን ጠብቆ መከናወኑን መከታተል፤

፮. በብሔራዊ ደረጃ የክሪፕቶሎጂ ጥናት፣ ዲዛይንና ዲቨሎፕመንት ሥራዎች በማከናወንና በቴክኖሎጂ ሽግግር አማካይነት ብሔራዊ የመረጃ ደህንነት ደረጃዎች መጠበቃቸውን ማረጋገጥ፤

፯. አለም አቀፋዊም ሆነ ሀገራዊ የኢንፎርሜሽን መረብ ሥርዓትን በመጠቀም በሀገሪቱ ህገ መንግሥታዊ ሥርዓትና ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ የሚቃጡ የወንጀልና ሽብር ተግባሮችን መከታተልና በአጥፊዎቹ ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መተባበር፤

፰. በኦፕቶሮኒክስ፣ በሪሞት ሴንሲንግ ቴክኖሎጂዎችና በሌሎች የአየርና የየብስ ቅኝት ሥርዓቶች አማካይነት ከመሬት በላይና በታች አመልካች ዳታዎች ለመሰብሰብ፣ ለመተንተን፣ ለማከማቸትና ለማሠራጨት የሚያስችል በጥናትና ምርምር የተደገፈ ስርዓት እንዲኖር ማድረግ፤

፱. የቁልፍ ተቋማትን ኔትወርክ፣ ሶፍትዌርና ሃርድዌር ቴክኖሎጂ አመራረጥ፣ የክሪፕቶሎጂ አልጎሪዝም ስታንዳርድ፣ ኮንፍግሬሽን፣ አጠቃቀምና ደህንነት በሚመለከት በምርምር የታገዘ ድጋፍ መስጠት፤



4. *Head Office*

The Agency shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5.. *Objective*

The objective of the Agency shall be to ensure that the country's use of information and information communication network technologies and telecommunication in the implementation of its peace, democratisation and development programs is without risk to the national security.

6. *Power and Duties*

The Agency shall have the powers and duties to:

1. advise the Government on information and information communication network security and monitor the implementation of approved policies and legislations;
2. create national research and development capability in information communication network technology and information warfare, and carry out research, development, design, testing and evaluation activities in collaboration with public and private institutions;
3. facilitate coalesced national approach in dealing with policy, legislative, knowledge and other issues relating to the use of computer network, information systems and electromagnetic energy and to information warfare;
4. provide research based capacity building support to various security agencies and institutions on signal intelligence, technical intelligence and cryptology;
5. monitor the collection, processing and dissemination of remotely sensed data using remote sensing, magnetic field, gravity survey and electro-optical sensors and handling of geo-spatial information databases to ensure their compliance with national information security standards;
6. ensure the enforcement of national information security standards through national cryptology research, design and development and technology transfer;
7. monitor acts of crime and terror waged against the country's constitutional order and national interests using international or national information communication network systems, and cooperate with the concerned authorities in taking legal actions against the offenders;
8. create research and development based facilities to utilize optronics, remote sensing technologies and other air and ground based survey systems for surface and sub-surface information collection, processing, storing and dissemination;

፱. የቁልፍ ተቋማትን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አጠባበቅ ጥንካሬና ተጋላጭነትን ለመለካት የሚያስችል የሪስክ አሰስመንት ጥናትና የሙከራ ሥራ መሥራትና የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ማገዝ፤

፲. በመንግሥታዊም ሆነ በግል ተቋማት ሀገራዊ ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥል ተጋላጭ ጎኖችን ለመከላከል የሚረዳ ከፌደራል የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ የኢንፎርሜሽን ሴኩሪቲ ፖሊሲ፣ ስታንዳርድና ፕሮሲጀር እንዲዘጋጁና እንዲተገበሩ መደገፍ፤

፲፩. የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አጠባበቅ ንቃተ ህሊናን የሚያሳድጉ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች መቅረጽና መስጠት፤

፲፪. ወደ ሀገር የሚገቡና ከሀገር የሚወጡ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን፣ የመረጃ ሴንሰሮች፣ የኢንፎርሜሽን ጦርነትና የክሪፕቶሎጂ ቴክኖሎጂዎች ከብሔራዊ ደህንነት አንጻር ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋ ከሌሎች የመንግሥታዊ የፀጥታ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መከታተል፤

፲፫. ብሔራዊ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነትን በተሟላ መልኩ ለመጠበቅ የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት፤

፲፬. ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ ማስከፈል፤

፲፭. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ፤

፲፮. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን፡፡

፯. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፣

፩. እንዳስፈላጊነቱ በመንግሥት የሚሰየም አማካሪ ቦርድ፣

፪. በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

፫. አስፈላጊው ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

፰. <u>የዋናው ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. ዋናው ዳይሬክተር የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋናው ዳይሬክተር፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎችን መሠረታዊ ዓላማዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኤጀንሲው በተፈቀደለት በጀት መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ) የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርቶች ያዘጋጃል፡፡



9. provide research and development based support to critical infrastructure with respect to the selection, cryptology algorism standards, configuration, use and security of network, software and hardware technologies;
10. undertake risk assessment studies and testing activities to evaluate reliability and vulnerability of the information communication network security systems of critical infrastructures and provide support in taking corrective measures;
11. prevent threats to the national security, provide support to public and private institutions in the formulation and implementation of information security policy, standards and procedures in conformity with the federal information security policy;
12. design and implement awareness creating educational and training programs on safeguarding information communication network security;
13. monitor, in collaboration with other security organs, national security threats connected with the import and export of information communication, information sensor, and information warfare and cryptology technologies;
14. ensure that the manpower required to safeguard the national information communication network security is provided with appropriate training;
15. charge commensurate fees for the services it renders;
16. own properties, enter into contracts, sue and be sued in its own name;
17. perform other acts as are required for the attainment of its objective.

7. *Organization of the Agency*

The Agency shall have:

1. an Advisory Board to be designated by the Government as may be necessary ;
2. a Director General and Deputy Director Generals to be appointed by the Government; and
3. the necessary staff.

8. *Powers and Duties of the Director General*

1. The Director General shall be the chief executive officer of the Agency and shall direct and administer the activities of the Agency.
2. Without limiting the generality stated in sub-article (1) of this Article, the Director General shall:
   (a) exercise the Powers and duties of the Agency specified under Article 6 of these Regulations;
   (b) employ and administer the employees of the Agency in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;
   (c) prepare the work program and budget of the Agency and implement same upon approval;
   (d) effect expenditure in accordance with the approved budget of the Agency;
   (e) represent the Agency in all its dealings with third parties;
   (f) prepare the operational and financial reports of the Agency

፫. ዋናው ዳይሬክተር ለኤጀንሲው የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

፱. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ከሚመደብ ገንዘብና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮(፲፭) መሠረት ከሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያ የሚውጣጣ ይሆናል፡፡

፲. <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

፩. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

፲፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር



3. The Director general may delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the Agency to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Agency.

9. *Budget*

The Agency's budget shall be drawn from funds allocated by the Government and service fees to be collected pursuant to Article 6 (15) of these Regulations.

10. *Books of accounts*

1. The Agency shall keep complete and accurate books of accounts.
2. The books of accounts and financial documents of the Agency shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

11. *Effective Date*

These regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit gazeta done at Addis Ababa, this 15th day of Dec. 2006.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA